# ህወሓት ለምን ኢትዮጵያን ወደብ-አልባ ማድረግ መረጠ?

ከታምሩ ለታ

*May 25, 2016*

የኢትዮጵያን ያህል ሕዝብ ብዛት ይዞና የኢትዮጵያን ያህል ለባህር ቀርቦ ወደብ-አልባ ሀገር በአለማችን የለም::ብዙ ወደብ-አልባ ሀገሮች ለወደብ-አልባነት የበቁት ከባህር አጅግ ርቀው በመኘታቸው ነዉ:: እንደምሳሌ ያህል ቻድ፣ ድቡብ ሱዳን እና ዩጋንዳ ከአፍሪካ; ፓራጉዋይ ከላቲን አሜሪካ; ሞንጎሊያ ከእስያ መጥቅሰ ይቻላል:: እኘህ ሀገሮች ከባህር በጣሙኑ ርቀዉ ነዉ የሚገኙት:: ስለዚህ ለኘህ ሀገሮች ወደብ-አልባነት ተፈጥሮ የጫነችባቸዉ መልከአምድራው አጣፈንታ ነዉ። በአንጻሩ ኢትዮጵያን የተመለከትን እንደሆነ ለቀይ ባህር በጅጉ የቀረበች ሀገር ናት። የአሰብ ውደብ ከኢትዮጵያ ድንበር ያለዉ ርቀት አዲስ አበባ ክብሾፍቱ (ደብረዘይት) ካላት ርቀት ጋር ተመጣጣኝ ነዉ። ይህን ያህል ለባህር ቀርቦ ወደብ-አልባ የሆነ ሀገር በአለማችን የለም። ይልቁንም እንደ ኮንጎ ያሉ ከባህር የራቁ ሀገሮች ድንበር ስንመለከት ወደባህር የሚያሳልፍ ኮሪደር ባለቤት ሆነዉ አናገኛቸዋለን። የህወሓት ዉሳኔ ኢትዮጵያን ለባህር በጅጉ ቀርባ ወደብ አልባ የሆነች ብቸኛዋ ሀገር አርጉዋታል።:

## Asab Port

ወደብ-አልባ ሀገር መሆን ያመጣበንን ጣጣ በበዙዉ አይተናል። በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ብዙ ኢትዮጵያውያን ነጋዴዎች ንብረታችዉን ወደብ ላይ ተወርሰዋል። ጅቡቲ ደርሳ ባታስጥለን ኖሮ የዓለም-ንግድ አንገታችን ተቆርጦ ነበር። ከዓለም ንግድ መቆረጥ እንደምታዉ ቀላል አይደለም። በድርቅ ሳቢያ የተራቡ ወአኖቻችንን ሕይወት ለማዳን እንኩዋን ስንዴዉ ከዉጪ መምጣት አለበት። ለዘወትር ፍጆታችን የምንጠቀምባቸዉ መሰረታዊ ነገሮችም (መድሃኒትና ነዳጅን ጨምሮ ) ዞዎቹ ከዉጭ መምጣት አለባቸው። ከጅቡትም የደረሰልን የነብስ-አድን አስተዋጽኦ በነጻ የተገኘ አይደለም — ሕዝብ እጅግ ደክሞ ያፈራዉን ሃበቱንና ሉዓላዊነቱን ገብሮበታል። ለወደብ ኪራይ የሚከፈለው ገንዘብ ማንንም ወገን የሚያስደነግጥ ነዉ። በየአመቱ ኢትዮጵያ ለወደብ ኪራይ የምትፈጽመዉ ክፍያ ከመንግስት አፊሲዬላዊ ምንጮች ለማወቅ ባይቻልም (ሆን ተብሎ በድብቅ የተያዝ ይመስላል) ቢያንስ አንድ ቢሊየን ዶላር እንደሚሆን ይገመታል። ይህ የገንዘብ መጠን ቁጥር አንድ የሆነዉ የኤክስፖርት ምርታችን ቡና ከሚያስገኘው ገቢ ይበልጣል። መላዉ የኢትዮጵያ ቡና አምራች ገበሬ ለፍቶ አምርቶ፤ ነጋዴዉ ደክሞ ሰብስቦ ለሃገሩ ያስግኘዉ ሃብት ሙሉ በሙሉ ለወደብ ክፍያ ይዉላል!! ያም ስለማይበቃ ተጨማሪ ገንዘብ ያስፈልጋል። ከዚያም አልፎ-ተርፎ ኢትዮጵያን ብሄራዊ ክብራችንን እና ሞራላችንን በሚነካ ደረጃ የጅቡቲ አጎብዳጅ እንድትሆን አስገድዷታል።

የህወሃት ሰዎች የሰጡን መልስ “ለኢትዮጵያ ብልጽግና ወደብ ያለዉ ፋይዳ እምብዛም አይደለም” የሚል ነው። ኤርትራ ስትገነጠል ኢትዮጵያ የወደብ-ይገባኛል ጥያቄ ብታስነሳ በሁለቱ ሃገሮች መሃል ግጭት ሊቀሰቅስና አላስፈላጊ ጦርነት ሊያስነሳ ይችላል። ወደብ ብዙም ፋይዳ ከሌለዉ ደግሞ ከኤርትራ ጋር የድንበር እሰጣገባ ዉስጥ መግባት ከጥቅሙ ጉዳቱ ሊያመዝን ይችላል የሚል ነው።

“ለኢትዮጵያ ብልጽግና ወደብ ያለዉ ፋይዳ እምብዛም አይደለም” የሚለዉ መከራከሪያ የህወሃት/ኢህአዴግ ሰዎች ሽንጣቸዉን ገትረዉ የተከራከሩበት ነዉ። ይህ መከራከሪያ ዉሃ የማያነሳ መሆኑን ለማሳያ ከላይ የጠቅስኩዋቸዉ የወደብ-አልባነታችን መዘዞች ብቻ በቂ ናቸዉ። ወደብ-አልባነት አንድን ሃገር ክፉኛ እንደሚጎዳ እንኩዋንስ ሃገር መራለሁ ብሎ የተደራጀ ቡድን ይቅርና ማንም ተራ ዜጋ የሚገነዘበው ጉዳይ ነዉ። ኢኮኖሚስቶችም ለበርካታ አመታት ባደረጉዋቸዉ ጥናቶች ወደብ-አልባነት የሃገሮችን የብልጽግና እድል እንደሚያቀጭጭ በማያሻማ ሁኔታ የተደመደመበት ጉዳይ ነዉ። ኢትዮጵያ ወደብ-አልባ እንዳትሆን በግዜዉ በርካቶ ምሁራን ጩሀታቸዉን ለህወሃት/ኢሃዴግ አሰምተዋል። የተሰጣቸዉ ምላሽም ከስራ መባረርና ከሃገር መሰደድ ነበር (ከስራ የተባረሩ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰሮችን ያስታዉሷል)።

ስለዚህም ህወሃት/ኢሃዴግ ኢትዮጵያን ወደብ-አልባ ያደረገዉ የወደብን ጥቅም ሳይገነዘብ ቀርቶ ነዉ ለማለት ያስቸግራል።ነገሩ በቀጥታ የማይመለከታቸዉ የወቅቱ የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ጂሚ ካርተር እንኩዋን መለስ ዜናዊን ኢትዮጵያን ወደብ-አልባ ከማድረግ እንዲታቀብ አደራ-መሰል ማሳሰቢያ ሰጥትዉት ነብር። ኢትዮጵያን ወደብ-አልባ ማድረግ የሩቁን ጂሚ ካርተርን የቆረቆራቸዉን ያህል መለስን

አልቀረቀረዉም። ስለወደብ አስፈላጊነት የተናገሩ ምሁራንን ማሰሩንና ማሳደዱን ለተመለከተ፤ ህወሃት/ኢሃዴግ በርገጥም ኢትዮጵያን ወደብ-አልባ አድርጎ የማስቀርት ጽኑ ፍላጎት እንደነበርዉ ያሳያል። ህወሃት የረጅም ግዜ ግቡን በጥንቃቄ የሚተልም ድርጅት ነዉ። በክፋቱ፤ በጭካኔዉ፤ በአምባ-ገነንነቱ ሊኮነን ይችላል። የሚፈልገዉን ባለማወቅ ግን አይታማም። ግቡን ለመምታትም ምንም ከማድረግ ወደ-ሁዋላ አይልም። መታሰር ያለበት ይታሰራል፤ መደብደብ ያለበት ይደበደባል፤ መገደል ያለበትም ይገደላል።

ህወሃት ለዚህ ዉሳኔ እንዲበቃ (ማለትም ኢትዮጵያን ወደብ-አልባ ለማድረግ) ያነሳሳዉ ምክንያት ምንድነዉ? በዚህ ጽሁፌ ለማሳየት የምሞክረዉ የህወሃት (ኢትዮጵያን ወደብ-አልባ ያደረገበት) ዉሳኔ ከሚከተሉት ሁለት መሰረታዊ የህወሃት ግቦች የሚመነጭ እንደሆን ነው።

1 ኛ፡ ህወሃት ኢትዮጵያን እንደ አንድ ጠንካራ ሀገር ለረጅም ግዜ የመግዛት ራእይ የለዉም። እስከተቻለዉ ድረስ የኢትዮጵያን ህዝብ ከፋፍሎና አንድነቱን አዳክሞ ይገዛል።

2 ኛ፡ የኢትዮጵያ ህዝብ ህወሃትን በቃኝ ባለ ግዜ የህወሃት ገዢዎች ትግራይን ተቆጣጥረዉና ከኢትዮጵያ በሃይል ገንጥለዉ ገዢነታቸዉን በትግራይ ክልል ይቀጥላሉ።

ህወሃት ከላይ የጠቅስኩዋቸዉን ሁለት የረጅም ግዜ ግቦች ይዞ እንደሚንቀሳቀስ ብዙም የሚያከራክር አይመስለኝም። ህወሃት ከጅምሩም ቢሆን ጫካ ሲገባ የትግራይን መንግስት መመስረት አላማዉ እንደነበር በመመስረቻ ሰነዳቸዉ ሳይቀር ያስቀመጡት ጉዳይ ነዉ። የማታ ማታ የደርግን መዉደቅ ተከትሎ አቅም አገኙና ኢትዮጵያን ለግዜዉም ቢሆን መቦጥቦጥ እንደሚችሉ ሲረዱ ተለጣፊ ፓርቲዎችን አቋቁመዉ መላዉ ኢትዮጵያን በከፋፍለህ-ግዛ ስትራቴጂ ተቆጣጠሩ። ስለዚህም ኢትዮጵያን መግዛት ከጅምሩ የወጡነት አላማ ሳይሆን ይኋላ-ኋላ አጋጣሚ የፈጠረላቸዉ ችሮታ ነዉ። በዘላቂነት እንደማያስኬዳቸዉም ከማንም በላይ ያውቁታል።

የኢትዮጵያ ህዝብ የህወሃትን አገዛዝ በቃኝ የሚልበት ግዜ እንደሚመጣ ህወሃት ጠንቅቆ ይገነዘባል። ለዚያ ግዜ ያስቀመጠው ካርዱ ደግሞ ኢትዮጵያን መበታተን እና ትግራይን ገንጥሎ መግዛት ነው። ይህን አካሄዳቸዉን በምርጫ 97 ማግስት የህወሃት ስልጣን ሲንገዳገድ አቶ መለስ ቁልጭ አድርጎ አሳይቶናል። ስብሃት ነጋም ቪኦኤ ላይ ቀርቦ ህገ-መንግስቱ ከተናድ (ማለትም ህወሃት ኢትዮጵያን ካልገዛ) እንደምንገነጣጠል ደግሞ ደጋግሞ አስጠንቅቆናል።

እናም ኢትዮጵያ የወደብ ባለቤት መሆኑዋ ከላይ ከጠቅስኩዋቸዉ ሁለቱ የህወሃት ግቦች ጋር በጅጉ ይጻረራል። ኢትዮጵያ የወደብ ባለቤት ከሆነች የህዝቦችዋ የአንድነት ፍላጎት ይጠናከራል። ምክንያቱም ከኢትዮጵያ እገነጠላለሁ የሚል ክልል (አፋር ሲቀር) ወደብ-አልባ ሆኖ ነዉ የሚቀረዉ። ወደብ ለመጠቀምም “አልፈልግሽም” ብሎ በተገነጠላት ኢትዮጵያ ላይ ጥገኛ ይሆናል። የትኛዉም ክልል ይህን እያወቀ የመገንጠል ፍላጎት ይኖረዋል ለማለት ይከብዳል። በመሆኑም ኢትዮጵያ የወደብ ባለቤት ብትሆን ኖሮ የህዝቦችዋ የአንድነት ፍላጎት ይበልጡኑ ይጠናከራል። ይህ ደግሞ ከላይ ከጠቀስኩዋቸዉ ሁለቱ የህወሃት ግቦች ጋር በጅጉ የሚጻረር ነው። አንደኛ ህወሃት የኢትዮጵያን ህዝብ አንድነት አዳክሞና ከፋፍሎ ለመግዛት ይበልጥ ያስቸግረዋል።

ሁለተኛ፤ ወደቡ በኢትዮጵያ እጅ መሆኑ ትግራይን ከኢትዮጵያ የመገንጠል የረጅም ግዜ ግቡን አስቸጋሪ ያደርግበታል። የትግራይ ህዝብ ከኢትዮጵያ ተገንጥሎ ዳግመኛ ለወደብ አገልግሎት ኢትዮጵያ ላይ ጥገኛ እንደሚሆን ሲገነዘብ በህወሃት የመገንጠል አጀንዳ ላይ ያለዉ ተቃዉሞ ይበረታል። አንድነቱ የተጠናከረዉ ሌላዉ የኢትዮጵያ ህዝብም የህወሃትን አጀንዳ ለማደናቀፍ (ሃይል መጠቅምን ጨምሮ) የተሻለ አቅም ይኖረዋል። ህወሃት ይህን ተቃዉሞ አልፎ እንኩዋን ትግራይን ቢገነጥል፤ ከኢትዮጵያ ጋር በጠላትነት የሚለያይ ሆኖ ሳለ ለወደብ አገልግሎት ግን ኢትዮጵያ ላይ ጥገኛ ይሆናል።

ስለዚህም ወደቡ ወደፊት በሚገነጠላትና የለየላት ባላንጣዉ በምትሆነዉ፤ እንዲሁም አንድነቱዋ በጠነከረዉ ኢትዮጵያ እጅ መሆኑ ለህወሃት ማራኪ አማራጭ አልነበርም። ይልቁንም ወደቡ ያኔ ወዳጁ በነበረዉና (ወደፊትም ጸበኛዬ ይሆናል ብሎ ባልጠበቀው) ሻቢያ እጅ እንዲቀመጥ መረጠ። ያ የከፉ ቀን መጥቶ የኢትዮጵያ ህዝብ ቢነሳ፤ አንድነቱዋ የተዳከመዉና ወደብ-አልባዋ ኢትዮጵያ ትተራመሳልች፤ ትበታተናለች። ህወሃት ኢጋዚ ጦሩን ይዞ ትግራይን ይቆጣጠራል። የትግራይ ህዝብም የኢትዮጵያን ትርምስ ከመቀላቀል የህወሃት ጭሰኛ ሆኖና ቢያንስ የተረጋጋ የመንግስት ባለቤት ሆኖ ይቀጥላል። ህወሃትም የረጅም ግዜ ወዳጄ ነዉ ብሎ ባሰበዉ ሻቢያ እጅ ያለን ወደብ ቢያንስ ተከራይቶ መጠቀም ይችላል። ወደቡ በጠላትነት በተለያት ኢትዮጵያ እጅ ቢሆን የመከራየትም እድል አይኖረዉም።

እናም በዚህ ክፉ የህወሃት ሴራ 100 ሚሊዮን ህዝብ ለፍቶ ጥሮ ያፈራዉን ሀብት ለጅቡቲ ይገብራል። ለመላው አፍሪካና ጥቁር ህዝብ የነጻነት አርማ የሆነች ሃገር ወድብ ፍለጋ ምናልባትም ከአንድ ወረዳ ለማይበልጡ እንደ ጅቡቲና ሱማሌ-ላንድን ለመሳሰሉ ትንንሽ ሀገሮች ታጎበድዳለች። እንዲህ የሀገራችንን ጥቅም ባደባባይ የሚሸጥ ቡድን ቀጥቀጦ ሲገዛን ማየት ማንንም ኢትዮጵያዊ በቁጭት ማንገብገቡ አይቀርም። ያለዉም አማራጭ ሁለት በቻ ነዉ — ህወሃት በቀደደልን ቦይ ቁልቁል መንገዋለል ወይም የስልጣን ኮርቻዉን በሀይል ነጥቆ ፈረሱን በምንፈልገዉ አቅጣጫ መጋለብ።